**ወልቂጤ ዩኒቨርቲ**

# " ዮቶር 2" ረጅም ልብ-ወለድ ከረጅም ልብ-ወለድ አላባውያን አንፃር ትንተና

**በ**

**እግዜርደግ በለጠው**

**በማህበራዊ እና ስነሰብ ኮሌጅ ለቲአትር ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ**

**አርትስ ዲግሪ ማሙያነት የቅርብ ጥንታዊ ፅሁፍ**

**ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ**

**ታህሳስ 2017 ዓ.ም**

# "ዮቶር 2" ረጅም ልብ-ወለድ ከረጅም ልብ-ወለድ አላባውያን አንፃር ትንተና

በ

እግዜርደግ በለጠው

የጥናቱ አማካሪ

መምህርት ቤተልሄም አንጃ

# የአማካሪ ማረጋገጫ

የአማካሪው/ዋ ስም -------------------------------------

ፊርማ ---------------------------

ፈታኝ አንድ ፊርማ --------------------------

ቀን -------------------------------

ፈታኝ ሁለት ፊርማ-----------------------------

ቀን________________________

# አበርክቶ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ መታሰቢያነቱ ለወንድሜ ለአብርሃም መንግስቱ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

በመጀመሪያ ሀሉን ለፈጠረ ይህን ሁሉ እንዳከናውን ለረዳኝ እና እስከዚች ሰዓት ላቆየኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይሁንልኝ። በመቀጠል ስለ እኔ የኖረችው ለእናቴ ለእምዬ ምስጋና ይድረስልኝ። እንዲሁም ስህተቶቼን እያረመች በጥሩ ሁኔታ ጥናታዊ ፅሁፌን እንድሰራ ለረዳችኝ ለመምህርት ቤተልሄም አንጃ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው። በመጨረሻም ይሄን ጥናታዊ ፅሁፍ ስሰራ ከጎኔ ለነበርከው በለጠ ጥላሁን ከልብ አመሰግናለሁ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ከ አላባውያን አንፃር በመተንተን የሚያጠነጥን ነው። ሙሉ በሙሉ በልቦለዱ ውስጥ የአላባውያን አጠቃቀምን ይፈትሻል። ይህንንም በማድረግ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት መልስ ይሰጣል። ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ  በፀሀፊ አለማየሁ ደመቀ የተፃፈ ሲሆን ጥናቱን ሙሉ ለማድረግ ገላጭ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም የልቦለድ ምንነትንና የረጅም ልቦለድ አላባውያንን በመዘርዘር በልቦለዱ ላይ በምን እና እንዴት ተጠቅሟል የሚለውን ያሳያል። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የቶር 2 ረጅም ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ አላባውያን አንፃር ማለትም ከታሪክ፣ ከገፀ ባህሪያት፣ ከመቼት፣ ከጭብጥ፣ ከግጭት፣ ከአንፃርና ከትልም አንፃር በመተንተን ሂስ ያደርጋል። እነዚህን የረጅም ልቦለድ አላባውያንን በመጠቀም አላባውያንን እንዴት እንደተጠቀመና ያሉትን ችግሮች በማንሳት ለችግሮችም የራሱን መፍትሔ ሀሳብ አስቀምጧል።

## ማውጫ

ምዕራፍ አንድ....................................................................................................................1
1.1 መግቢያ.......................................................................................................................1
1.2 የጥናቱ ዳራ...................................................................................................................1
1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ...............................................................................................2
1.4 የጥናቱ አላማ................................................................................................................2
1.4.1 የጥናቱ አብይ አላማ..................................................................................................2
1.4.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ ...................................................................................................2
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ..........................................................................................................2
1.6 የጥናቱ ወሰን.................................................................................................................3
1.7 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ...........................................................................................3
1.8 የጥናቱ ዘዴ...................................................................................................................3
1.8.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች...............................................................................................4
1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች..........................................................................................4
ምዕራፍ ሁለት....................................................................................................................5
2. ክለሳ ድርሳናት....................................................................................................................5
2.1 ልቦለድ........................................................................................................................5
2.1.1 የልቦለድ ምንነት.........................................................................................................5
2.2 የልቦለድ አላባውያን.........................................................................................................5
2.2.1 ታሪክ.........................................................................................................................5
2.2.2 ገፀ ባህሪያት..................................................................................................................6
2.2.3 መቼት.........................................................................................................................7

2.2.4 ግጭት........................................................................................................7

2.2.5 ጭብጥ.......................................................................................................9

2.2.6 አንፃር.......................................................................................................9

2.2.7 ትልም.....................................................................................................12

2.3 የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት.................................................................................12

ምራፍ ሶስት.......................................................................................................13

3.1 የመረጃ ትንተና...............................................................................................13

3.1.1 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ................................................................................13

3.1.2 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ትንተና.......................................................................14

3.1.2.1 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ታሪክ......................................................................14

3.1.2.2 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ የገፀ ባህሪያት አሳሳል......................................................15

3.1.2.3 ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ትልም.......................................................................19

3.1.2.4 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ መቼት......................................................................20

3.1.2.5 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ግጭት......................................................................21

3.1.2.6 ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ጭብጥ.......................................................................23

3.1.2.7 ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ አንፃር................. .........................................................24

ምዕራፍ አራት..... .................................................................................................25

4.1 ማጠቃለያ .........................................................................................................25

4.2 የመፍትሄ ሀሳቦች..................................................................................................25

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1.መግቢያ

ልብ- ወልድ በደራሲዉ  ምናብ ዉስጥ የራሱን ዓለም የገነባ ሀሳብ ተንሸርሽሮ በስነ-ፅሁፍ ለዛዉ የአንባቢያንን ቀልብ ሰቅዞ መያዝ የሚችል የገሀዱ ዓለም የሚንፀባርቅበት የስነ- ፅሁፍ ዓይነት ነዉ።ደራሲዎች የሰዉ ልጅ የማያነሳቸዉን ጥያቄዎችማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ ፤ ሀይማኖታዊ ፤ ፓለቲካዊ  እሲቶችን ለመጠቀም በልብ -ወልድ የአተራረክ ዘዴዎችን ለዓንባቢያን ያቀርባሉ። ልብ-ወለድ የፈጣሪዉን ምዕናብ ከግሀዱ ዓለም ጋር ዓዋህዶ በተለያዩ  የቋንቋ ዉበት ላላቸዉ ለፅሁፎች ተደራሲዉን ከነባራዊ ሁኔታዉየመነጠል አቅም ያለዉ የኪነ-ጥበብ ዓይነት ነዉ።ሁለት አይነት  ልብ-ወለዶች አሉ። ረጅም ልብ -ወለድ እና አጭር ልብ-ወለድ ።ረጅም ልብ-ወለድ ከአጭር ልብ-ወለድ በብዙ መንገድ ይለያያሉ። በረጅም ልብ-ወለድ  ዉስጥ የልብ- ወለድ አላባዉያን የሚባሉት ገፀ-ባህርያት ፣ጭብጥ ፣ ታሪክ ፣ መቼት ፣ ትልም ፣ አንፃር ፣ ግጭት በሰፊዉ የሚገኙና ለደራሲዉ ከፍታን ነፃነት የሚሰጡ ናቸው ። በአጭር ልብ-ወለድ ግን ታሪኩ፣ መቼቱ ፣ገፀ -ባህሪያቱ ፣ ግጭቱ ዉስን  እና የተገደቡ ናቸው ።እንዲሁም በተለያዩ የአፃፃፍ  ቴክኒኮች ይለያያሉ።

ዘ መና ዊ ው  የ ቲ ያ ት ር   ዘ መን   ከ ገ ባ   ጀምሮ  በሀገራችን  ብዙ  የአፃፃፍ  ስልቶችንና ቋንቋዎችን በመጠቀም ልብ ወለድ ሲፃፍ ኑሯል። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ወጣት ደራሲያን እና ሀያሲያን ብቅ ብቅ እያሉ እና የተለያዩ የስነ ፅሁፍ ችሎታቸዉን ለምሳሌ ግጥም፣ዓጫጭር ልብ ወለዶች ፣ረጅም ልብ ወለዶችን በመፃፍ ላይ ይገኛሉ።ለዚህም ከበፊት የነበሩ አንጋፋ ደራሲያን ዓሁን በሀገራችን የስነ -ፅሁፍ እንቅስቃሴ ላይ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸዉ በዚህ ትዉልድ አንፀባርቆ ይታያል።ስነ ፅሁፍ የፃፊዉን የፈጠራ አለም ለተደራሲዉ የሚያሸጋግር የኪነ -ጥበብ ድልድይ እንደመሆኑ ልብ -ወለድ ከዘመን ዘመን የአፃፃፍ ስልቱ እየተቀየረና ቅርፁን እየቀያየረ እዚህ ደርሷል።

## 1.2. የ ጥና ቱ ዳ ራ

አንድ ልብ- ወለድ በታሪኩ ዉስጥ እረጋ ብሎ የሚንሸራሸር ሴራ፤ግልፅ የሆነ አንባቢያን ግራ የማያጋባ የገፀ-ባህሪ አሳሳል ፤ከዋናዉ ጭብጥ ዉጭ ብዙ አብይ'ጭብጦችን የያዘ፤ለገሀዱ ዓለም ግልፅ የሆነ ወይም በፈጠራ ዉስጥ ድንቅ የሆነ የመቼት አገላለፅ፤አላማን ግጭቶች፤ዉብ በሆነ የቋንቋ አጠቃቀም እና አተራረክ ሲጠቀም ጥሩ ልብ-ወለድ ሊባል ይችላል። ረጅም ልቦለድ ብዛት ካላቸዉ ቃላትና ሀረጋት እንዲሁም አንድ አበይት ርዕስ ይዞ በዛ ርዕሰ ስር ሌሎች ንዑስ–አርዕስት በማካተት የፀሀፊዉን ልቦለዳዊ ስነ–ፅሁፍ  የሚቀርብበት የልቦለድ ዓይነት ነዉ። ረጅም -ልቦለድ ከሌሎች የስነፅሁፍ አይነቶች ጋር ብዙ የሚለይበት ነገር ቢኖርም። እንደ ልብ ወለዳዊነቱ ከአጫጭር ልብ ወለድ ጋርም የሚለያዩበት ነገሮች ይኖራል።  አጭር ልብ ወለድ እንደ ረጅም ልብ ወለድ ሁሉ፤ ታሪክ፣ ገፀ ባህሪያት፣ መቼት፣ ምክንያት እና ውጤት የመሳሰሉትን

አላባውያን አሉት። በርግጥ አጭር ልብወለድ እና ረጅም ልብ ወለድ የየራሳቸው የሚለያዩበት መንገድ አለ።ለምሳሌ ያህል አጭር ልብ ወለድ በጥድፊያ የተሞላ ነው፤ ረጅም ልብ ወለድ ግን ታሪኩን ጥግ ወስዶ የመመለስ፤ ሽቅብ ቁልቁል የማገለባበጫ እንዲሁም የተለያዩ አላባውያንን ያለ ገደብ የመግለፅ ነፃነት አለው።

## 1.3 የ ጥና ቱ አ ነ ሳ ሽ ምክ ን ያ ት

አጥኝው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማጥናት ያነሳሳበት ዋነኛ ምክንያት በ"ዮቶር 2"ረጅም ልብ-ወለድ ረጅም ልቦለድ  ከዚህ በፊት ጥናታዊ ፅሁፍ አለመሰራቱ እና ለንባብ ከበቃ አጭር ጊዜ በማስቆጠሩ ነው። እንዲሁም አጥኝዉ "ዮቶር 2" ረጅም ልብ-ወለድ ከረጅም ልብ-ወለድ አላባዉያን ዓንፃር ጥናታዊ ፅሁፍ  ለመስራት ያነሳሳበት ሌላኛው ምክንያት ልብ-ወለዱ  በሚገባ የልብ-ወለድ ባህርያትን ወይም ዓላባዊያንን ሁሉንም መጠቀሙን ለመፈተሽ ነዉ።

## 1.4. የ ጥና ቱ  ዓ ላ ማ

### 1.4.1 የ ጥና ቱ  ዓ ብይ  ዓ ላ ማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዓብይ ዓላማ "ዮቶር 2" ረጅም ልብ-ወለድ ከረጅም ልብ-ወለድ ዓላባዉያን ዓንፃር መተንተን ላይ ነዉ።

### 1.4.2 የ ጥና ቱ  ን ዑ ስ  ዓ ላ ማ

የዚህ ጥናታዊ  ፅሁፍ ንዑስ ዓላማ

፦ስለ ዮቶር 2 ረጅም ልብ -ወለድ  ታሪክ ማሳወቅ

፦ የልብ-ወለድ አላባዉያንን፤ገፀ-ባህሪ፤መቼት፤ሴራ፤ግጭት፤ጭብጥ፤ታሪክ፤ መተንተን

፦ ዮቶር 2 ረጅም ልብ-ወለድ ደካማ እና ጠንካራ ጎን መተንተን

## 1.5.የ ጥና ቱ  ጠቀ ሜታ

የዚህ ጥናታዊ  ፅሁፍ ጠቀሜታ፦

- ስለ ረጅም ልብ -ወለድ አፃፃፍ ግንዛቤ ይሰጣል።
- በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ  ዙሪያ መሰረት ለሚፈልጉ ሰዎች እንደ መነሻ እና እንደ አጋዥ መፅሀፍነት እንዲሁም

ስለ ረጅም ልብ-ወለድ ዓላባዉያን የተለያዩ መረጃዎችን ለዓንባቢያን ያደርሳል እንዲሁም

➤ ለዮቶር 2 ረጅም ልብ-ወለድ መፅሀፍ ላይ ተገቢ የሆነ መረጃ ከስነ-ፅሁፉ አንፃር ይስጣል።

➤ ለዮቶር 2 ረጅም ልብ-ወለድ አንባቢያን ከንባብ ባሻገር በስነ-ፅሁፋዊ ህግጋት አንፃር ተገቢውን እውቀት ስለ መፅሀፉ ያስጨብጣል።

## 1.6 የ ጥና ቱ ወሰ ን

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ወሰን "ዮቶር 2" ረጅም ልብ-ወለድ ከረጅም ልብ-ወለድ አላባዉያን ባህርያት አንፃር ማለትም ከታሪክ፣ ከትልም፣ ከጭብጥ፣ ከገፀ ባህሪያት፣ ከአንፃር፣ ከግጭት አንፃር ትንተና በመስጠት ላይ የተወሰነ ነዉ።

## 1.7 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከታች የተዘረዘሩ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡-

፡- ረጅም ልብ-ወለድ ምንድን ነዉ ?

፡- የረጅም ልብ-ወለድ አላባዉያን እነማን ናቸዉ እንዲሁም እንዴት መጠቀም ይቻላል ?

፡- በ"ዮቶር 2" ረጅም ልብ-ወለድ ዉስጥ ዓላባዉያን እንዴት ተቀርፀዋል ?

፡-የ "ዮቶር 2" ረጅም ልብ -ወለድ ከአላባዊያን ዓንፃር በአግባቡ ተገልጿል ?

## 1.8 የጥናቱ ዘዴ

ይህን ጥናታዊ ፅሑፍ ለመተንተን የሚጠቀመው ያጠናን ዘዴ ገላጭ ያጠናን ዘዴን በመጠቀም "ዮቶር 2" ረጅም ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ አላባውያን አንፃር ትንተና አድርጓል። ስለ ገላጭ የምርምር ዘዴ አለም እሸቱ "መሰረታዊ የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ላይ እንዲህ ሲል ያብራራዋል፡-

> ገላጭ ምርምር ገለፃ ትንታኔ እና አተረጓጎም መሠረት ያደረገ ምርምር
> ወይም የአጠናን ዘዴ ነው። በዚህ የአጠናን ዘዴ ለብዙ ጥናታዊ ፅሁፎች
> ጥቅም ላይ የዋለና በጥናቱ የሚነሱ ሀሳቦችን በተለዋዋጮች መካከል
> የሚፈጠሩ ተዛማጆችን ዕያወዳደረ የሚተነትን የሚያነፃፅር የአጠናን ዘዴ

ነ ው። (አ ለም እሸቱ፥1994፥65)

አጥኝው ይህን የአጠናን ዘዴ የመረጠበት የመረጠበት ምክንያት ጥናቱ በሰፊዉ እና በጥልቅ እንዲተነተን ስለሚያግዘዉ ነው ።

### 1.8.1. የመረጃ አሰባስብ ዘዴዎች

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ሁለተኛ እጅ የመረጃ ማግኛ ዘዴ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን። ይህም ዘዴ በሌላ ሰው ምርምር ወይም ልምድ ላይ ተመስርተው መረጃን የሚያቀርብ ሁለተኛ እጅ ምንጭ ይባላል። በዚህም ዘዴ ሰፋ ያለ ትንተና የሚያቀርቡ እና ምሁራዊ ጽሑፎችን እና የመማሪያ መጽሃፎችን፣ ጥናታዊ ፅሁፎች መፅሀፍት ያካትታሉ። አጥኝውም ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አንፃራዊ ትንተና መረጃ ለማሰባሰብ ቀላሉና አመቺ ዘዴ ሆኖ ስላገኘዉ ዮቶር 2 ረጅም ልብ-ወለድን ከረጅም ልብ-ወለድ አንፃር ተንትኖበታል።

## 1.9.በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

አጥኚው ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ በሚያጠናበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በዋናነት፡-፡

የተለያዩ ለመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉ መፅሀፎቶች በአቅራቢያ አለመኖር በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ሲሆኑ እነዚህን ያጋጠሙ ችግሮች ከጥናታዊ ፅሁፉ አማካሪ እና ከክፍል ጎደኞቹ ጋር በመነጋገር ሌሎች መፍትሄዎች የተወሰደ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉ የተለያዩ መፅሀፍትና ተዛማጅ ፅሁፎችን ከሌሎች ቦታዎች በመፈለግ ጥናቱን ሙሉ ለማድረግ ተሞክሯል።

# ምዕራፍ ሁለት

# 2 ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ልብ ወለድ

### 2.1.1 የልቦለድ ምንነት

ልቦለድ ማህበራዊ ህይወትን በስፋት በሚጥምና በሚስብ ዘይቤ የማሳየት አቅም ያለዉ የሰዉን ልጅ አያሌ ገጠመኞችን ማቅረብ የሚችል ኪነ -ጥበባዊ ቅርዕ ነዉ:: ከሌሎች የስነ - ፅሁፍ ዘርፎች የበለጠ ዘላቂነት ያላቸዉ የተስፋፉና የበለፀጉ የሰዎች ምስሎችን የመያዝ አቅም አለዉ። በልብ ወለድ የሰዉ ልጅ ሀዘን ደስታ፣ጥላቻ ፍቅር ፣ ምኞት ፍላጎት ፣ ብልፅግናና ዉድቀት በአጠቃላይ እይታውን በኪነታዊ ዘዴ ይቀርባል:: የልቦለድ ደራሲ የሰዉን የተለያዩ የሒወት ፈርጆች በኪነታዊ ቋንቋ በሚያቀርብበት ጊዜ የራሱን አመለካከት በመመርኮዝ ነዉ "ልብ ወለድ ደራሲዉ ለህይወት የሚሰጠዉ የግል ትርጓሜ ነዉ።" ( ዘሪሁን አስፋዉ ፣ 2005፣ 154)

## 2.2 የ ል ብ -ወ ለ ድ አ ላ ባ ዊ ያ ን

የተለያዩ  የኪነ-ጥበብ  ስራዎች በዉስጣቸዉ የሚዋሃዱበት ወይም መሰረታቸዉ የሚዋቀርበት ስርዓት  እንዳላቸዉ ሁሉ ልብ- ወለድም  ሰባት አላባዉያንን መሰረት ተደርጎበት  ይፃፋል። እነርሱም ገፀ -ባህሪ ፣ መቼት ፣ ታሪክ ፣ ግጭት ፣ ትልም ፣ አንፃር ፣ ጭብጥ ናቸው ። አንድ ልብ -ወለድ እነዚህን ሰባት አላባዊያኖች ማሟላት ካልቻለ ልብ - ወለድ ሊባል አይችልም። "የልብ- ወለድ አላባዉያን ለአንድ ልብ-ወለድ አስፈላጊ እና መሰረታዊ ናቸው ። ለልብ-ወለድ የልብ-ወለድ አላባዉያን የምንላቸዉ የልብ-ወለድ አከርካሪ አጥንት ናቸው። (ዘሪሁን አሰፋዉ ፣ 2005፣ 154)

### 2.2.1 ታሪክ

ታሪክ ማለት የልቦለድ ዋና ክፍል የሚይዝ ሲሆን የተለያዩ አንባቢያንን የሚይዝልን የልቦለድ የጀርባ አጥንት ነው።ታሪክ ደራሲዉ በመረጠዉ የጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ተቀናጅተዉ የሚያቀርቡትንና በገፀ-ባህርያቱ የሚፈፅሙትን ድርጊቶች አነሳስ ፣አፈፃፀምና የመጨረሻ ዉጤት ይይዛል። እነዚህ ሁሉ የስዉ ልጅ ልዩ ልዩ ገጠመኞች የተቀዱ መሆን ይኖርባቸዋል:: "ቅጅዉ በእዉነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ የታሪኩ ታአማኒነት ከፍ ያለ ይሆናል። የታሪክ ታአማኒነቱ ብቻ ሳይሆን አጓጊነት ሊኖረዉ ይገባል።" ( ዘሪሁን አሰፋው ፤ 2005፤ 156 )

## 2.2.2 ገፀ-ባህሪያት

ገፀ ባህሪያት በልብ ወለድ ውስጥ ደራሲው የፈጠረውን ታሪክ ተሸክመውልን የሚጓዙና እንደ ታሪኩ የየራሳቸው የአሳሳል ጥበብ ያረፈባቸው አካላት ናቸው። ገፀ ባህሪያት ከገሀዱ አለም ቢወሰዱም ወይም ከደራሲው ምዕናብ ውስጥ ቢፈልቁም የገሀዱ አለም አምሳያዎች ናቸው። አማረ ማሞ " የልብ ወለድ ድርሰት አፃፃፍ መሰረታዊ መመሪያዎች" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ ገፀ ባህሪያት እንዲህ ሲል አስፍሯል።

> ባለታሪክ፣ ገፀባህሪ ሴት፣ ወንድ ፣ሕፃን ፣ሽማግሌ፣ባልቴት በአንድ
>
> ልበለድ ታሪክ ውስጥ የራሳቸውንኑሮመኖርጠባያቸው፣ ስሜታቸውን
>
> በሚመራቸው መንገድ መሄድ የሚያምኑበትን ተግባር መፈፀም እንዲችሉ
>
> ደራሲ ተጨንቆ ተጠቦ የሚፈጥራቸው የታሪኩ ድርጊት ተሳታፊዎች
>
> ናቸው።(አማረ ማሞ፤ 1968፣30)

ገፀ ባህሪያት በልብ ወለድ ታሪክ ውስጥ ደራሲው ከታሪኩ ጋር በሚገባ እንዲዋሀዱ አድርጎ እንደሰጣቸው ድርሻ እና በታሪኩ ውስጥ እንዳላቸው አስተዋጽኦ በተለያዩ የአሳሳል ደረጃዎች ይካተታሉ። ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ ገፀ ባህርያት አሳሳል ሲገልፅ

> ሀበርት ሀፍነር የተባለው የንድፈ-ሃሳብ ሰው የገፀ ባህሪያት የአሳሳል
>
> ደረጃዎችን አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ እና ሞራላዊ በማለት
>
> ከአንደኛ እስከ አራተኛ የአቀራረፅ ደረጃዎች በመስጠት በቅደም
>
> ተከተል ያስቀምጣቸዋል። እነዚህ አራቱ የአሣሣል ደረጃዎች ነባራዊና
>
> ህሊናዊ የአሣሣል ደረጃዎች በሚሉ ትልልቅ መደቦችም ይከፈላሉ::
>
> አካላዊና ማህበራዊ የአሣሣል ደረጃዎች በአንድ አይነት መለኪያ
>
> ወይም ቁጥር ሊገለፁ ስለሚችሉ ነባራዊ የአቀራረፅ ደረጃዎች በሚል
>
> ይታወቃሉ። ሥነ-ልቦናዊና ግብረገባዊ መለያ ባህሪያት ደግሞ ቀጥተኛ
>
> መለኪያ ከማይገኝላቸው ላይ የተመሠረቱ ስለሚሆኑ በህሊናዊ የአሣሣል
>
> ደረጃዎች ሥር ይመደባሉ፡( ፋንታሁን እንግዳ፤ 2005፣25-2)

ከዚህ እንደምንረዳው ከገፀ ባህሪያት የአሳሳል ደረጃዎች ውስጥ ዋነኛው እና ቀዳሚ ቦታ የሚሰጠው አካላዊ የአሳሳል አይነት መሆኑን እና እንዲሁም ደግሞ ሞራላዊ እና ስነ ልቦናዊ አሳሳል የገፀ ባህሪያቱ ውስጣዊ ማንነቱ በመሆናቸው በህሊናዊ አሳሳል ደረጃ አስቀምጧቸዋል።

## 2.2.3 መቼት

መቼት ልበለዱ የሚከናወንበት ጊዜና ቦታ ነው።ቃሉ የሁለት ቃላት ጥምረት ሲሆን "መቼ"ድርጊቶች የተከናወኑበት ጊዜ የሚያመለክት ሲሆን "የት" ድርጊቶች የተከናወኑበትን ቦታ የሚያመለክት ነው።መቼት አጠቃላይ፣ ውስን ወይም ጥልቅ በሆነ መልኩ ሊቀርብ ይችላል። ዘሪሁን አስፋው" የስነ ስሁፍ መሰረታውያን" በሚለው መፅሀፉ መቼትን እንዲህ ሲል ገልፆታል፡-

> የልብ ወለድ ገፀ ባህርያት እውኑ አለም ሰዎች የመኖሪያ አከባቢ አላቸው በልብ ወለድ አለማማቸው የሚንቀሳቀሱት እና ታሪካቸውን የሚፈጽሙበት ደራሲው በመረጠው በተወሰነው አካባቢ ሲሆን የሚኖሩበትና ታረካቸውን የሚፈጽሙበት ታሪካዊ ጊዜ ወቅት እለትና ሰአትም ይኖራቸዋል። ይህ የገፀባህርያቱ መገኛ ስፍራና ጊዜ በአንዴነት መቼት ይባላል። መቼት ታሪኩ የተከናወነበትና ገፀ ባህርያቱ የሚኖሩበት ውይም የሚኖሩበት የገጠር ወይም የከተማው አከባቢ ብቻም አይደለም አያሌ ነገሮችን ይጨራሌ .ከገጠሩና ከከተማው ህይወታዊ እንቅቃሴ ጋር ያለትን የተለያዩ ሁኔታዎችን አካቶበመያዙ ዓዘ ብዙ ነው፡(ዘሪሁን አስፋው፣2005፣179)

መቸት የአንድ ልብ-ወለድ ታሪካዊ አዉድ እንዲሁም ለአጠቃላይ ዉስጣዊ መዋቅሩን ሊገልፅ እና ሊወክል የሚችል ተደርጎ ይፃፋል።መቼቶች የደራሲዉ ምዕናብ ሊፈጠሩ ወይም ደግሞ ከገሀዱ ዓለም ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ።ፈንታሁን እንግዳ "የተዉኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፍ ሰለመቼት አገባብ ሲገልፅ እንዲህ ይላል "በመቼት ገለፃ ዉስጥ አገባብ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። እነዚህ ታሪካዊ አገባብ ፤ መልካም ምድራዊ አገባብ ፤ የተፈጥሮ ክስተቶች አገባብ ናቸው።"(ፋንታሁን እንግዳ ፤ 2005 ፤ 11)

## 2.2.4 ግጭት

ግጭት የምንለው የልብ ወለድ አላባውያን ከሆኑት ውስጥ እንዱ ሲሆን ግጭት ወይም እርስበእርስ መነታረክ መጨቃጨቅ የሚለውን ትርጉም ይይዛል። ግጭት በአንድ ልብ ወለድ ውስጥ የሚኖሩ

ገጸባሪያት የሚያደርጉት የእርስ በእርስ ግጭት ወይም አለመግባባት ነው። ዘሪሁን አስፋው "የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን አተገባበር" በሚለው መፅሀፉ ግጭትን እንዲህ ገልፆታል፡-

> ግጭት በሁለት ተቃራኒ ሀያላት መካከል ሌላውን ለማሸነፍ ሌላውን
>
> ለመጣል ወይም አንዱ በሌላው ላይ የበላይነት ለማግኘት ሲጥር
>
> ሌላው ደግሞ ለማሸነፍ ለመውደቅ ወይም ላለመበለጥ ሲፍጨረጨሩ
>
> ይታያል ግጭት ገፀባሕርያቱ ከገቡበት ፍልሚያ ማጥ ለመውጣት
>
> ሲጣጣሩ ሌላ ችግር ስደነቀርባቸው እንደገና ለማርገብ ሲሞክሩ
>
> የሚታይበት አይነተኛ ፍሬ ነው። (ዘሪሁን አስፋው፣2005፤172)

ከዚህ እንደምንረዳው በአጠቃላይ ግጭት ማለት ሰዎች ወይም ገፀ ባህሪያቶች በሀሳብ አለመግባባት እና ከገባበት ችግር ለመውጣት የሚያደርጋቸው ፍልሚያች ናቸው። በአንድ ልበለድ ውስጥ የተለያዩ ግጭቶች አሉት። እነሱም ሰዉ ከሰው ጋር፣ሰው ከራሱ ጋር ሰው ከተፈጥሮ ጋር እና ሰው ከፈጣሪው ጋር በመባል ይከፈላሉ።

## ሀ. ሰው ከእራሱ ጋር ግጭት

በልብ ወለድ ውስጥ ያሉት ገፀ-ባህሪያት ከራሳቸው ጋር በተለያዩ ጉዳዬች ዙሪያ ሲጣሉ፤ እራሳቸውን በጥፋተኝነት ስሜት ሲወቅሱ፤ በተለያዩ ጉዳዬች ላይ መወሰን አቅቷቸው አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ ከእራሳቸው ጋር ሊጣሉ ይችላሉ። ይህንን ዘሪሁን አስፋው "የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን እና አተገባበር" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ ሲል ገልፆታል። "ይህ ግጭት ሰው ከራሱ ጋር የሚያደርገው ህሊናዊ ወይም ስነልቦናዊ የሚባለው ግጭት ነው። ይህ አይነት ግጭት በአንድ ሰው ውስጥ በሚኖሩ ፍላጎቶች መካከል የሚፈጠር ቅራኔ ነው::" (ዘሪሁን አስፋው፣2005፤175)

## ለ. ሰው ከሰው ጋር ግጭት

ሰው ከሰው ጋር ግጭት ልብ ወለድ ውስጥ በሰፊው የሚገኝ የግጭት አይነት ነው። ገፀባህርያት እርስ በእርሳቸው በማህበራዊ፤ በፖለቲካዊ፤ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዬች ላይ ጥል ሲፈጥሩ እንዲሁም ገፀ ባህሪቶች እርስ በእርሳቸው ጥቅማቸውን የበላይነታቸውን ለማስቀደም ወይም ደግሞ መብታቸውን ለማስከበር ይጋጫሉ። ይህንን ዘሪሁን አስፋው "የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን እና አተገባበር" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ ሲል ገልፆታል።

> ይህ የግጭት አይነት በሰውና በሰው መካከል የሚፈጠረውና ሰው ከሰው
>
> የሚባለው ነው ። ማለትም ሁለት ሰዎች ባላቸው እምነት፣ፍላጎት፣ የአላማ

ወይም የአቋም እንዲሁም የአስተሳሰብና በስብዕና ልዩነት የሚፈጠር

ግጭት ነው። (ዘሪሁን አስፋው፣ 2005፤175)

## ሐ. ሰው ከተፈጥሮ ጋር ግጭት

ይህ የግጭት አይነት በልብ ወለድ ውስጥ ገፀ ባህሪያት ከተለያዩ የተፈጥሮ ክስተቶች ጋር እንዲሁም እንደሚከተሉት ሀይማኖት ከአማልክቶች ወይም ከፈጣሪያቸው ጋር የሚጋጩበት የግጭት አይነት ነው። ዘሪሁን አስፋው "የስነፅሁፍ መሰረታዊያን"በሚለው መፅሐፍ እንዲህ በማለት ያብራራል። "ሰው ከተፈጥሮ ክስተቶችና ገፅታዎች ጋር የሚጋፈጠው ነው::" ሰዎች ለመኖር ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች እና ተግባራት ከተፈጥሮ አካላት ጋር ይገናኛሉ:: (2005፣176)

## 2.2.5 ጭብጥ

ይህ የአላባዊ አይነት በልብ ወለድ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው ማዕከላዊ መልዕክት ነው። ጭብጥ አብይ ጭብጥ እና ንዑስ ጭብጥ በመባል ይከፈላል። አብይ ጭብጥ ማለት ልብ ወለዱ በዋናነት ትኩረት አድርጎ ሊነግረን የፈለገው መልዕክት ሲሆን ንዑስ ጭብጥ ደግሞ ልብ ወለዱ በገፀ ባህሪያት፤ በተጨማሪ  በታሪኮች፤ ወይም ደሞ በተለያዩ የአተራረክ ጥበቦች ጥቃቅን መልዕክቶች የሚተላለፍበት ነው። ደራሲው አንድን ሀሳብ ወይም ደሞ ከአንድ በላይ ታሪኮችን ፈጥሮ ገፀ ባህሪያቱን በተለያዩ ግኑኝነቶች ውስጥ አስገብቶ ልብ ወለዱን ሲያዋቅር በአብዛኛው ጊዜ መነሻው ይህ ማዕከላዊ ትኩረት ወይም ጭብጥ ነዉ።(ዘሪሁን አስፋው፤ 2002፤185)

## 2.2.6 አንፃር

አንፃር ማለት ደራሲው ልብ ወለዱን ለመተረክ የተጠቀመበት የአተራረክ ዘዴ ነው። ደራሲዎች እንደየ ታሪኮቻቸው ወይም ደሞ ለመፃፍ እንደ እንደሚመቻቸው አተራረክ ይፅፋሉ። አንፃር በአራት አይነት ይከፈላል እነሱም ሁለን አወቅ አንፃር፣ውስን አወቅ አንፃር፣ አንደኛ መደብ አንፃር እና ተውኔታዊ አንፃር ናቸው።

ማንኛውም ልብ ወለድ  በደራሲው እና በአንባቢው መካከል ሆኖ ሁነቶቹን የሚገልጽና የሚተረጉም አልፎ አልፎ በግልጽ አብዛኛውን ጊዜ ግን በውስጥ ታዋቂ የሚኖሩ የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚያቀርብ ተራኪ አለው። ተራኪው ታሪኩ የሚመለከተው ተሳታፎ ወይም ታሪኩ የማይመለከተው ታዛቢ ሊሆን ይችላል። ተሳታፊ ከሆነ ታሪኩ የእሱም ታሪክ በመሆኑ የራሱም ሆነ ከሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ገፀባህርያት ታሪክ መስለው አመለካከት ያቀርባል። ታዛቢ ከሆነ ደግሞ ዳር ቆሞ ያየውን እና የታዘበውን እንዳለ ነው የሚያቀርበው። (ዘሪሁን አስፈው 2005፣190)

### 2.2.6.1 ሁሉን አወቅ አንፃር

ይህ የአንፃር ወይም የአተራረክ አይነት ደራሲው በድርሰቱ ሁሉምን ውስጣዊ  እውነታዎችን የሚገለፅበት ነው። የታሪኩ እያንዳንዱ ክስተቶች፤ የገፀባህሪያት ውጫዊ ሆነ ውስጣዊ ማንነታቸው ካለ ምንም ገደብ በነፃነት ለመተረክ የሚረዳ የአተራረክ ዘዴ ነው።

ቃሉ እንደሚያመለክተው ተራኪው በሌብ ወለድ ውስጥ የሚከናወነውን ሁለ የገፃባህሪያቱን በሌብ ወለድ ህይወተቸው የሚያጋጥማቸውን እጣ ፈንታ በውል የተገነዘበና ሚስጥራቸውን በዝርዝር የሚያውቅ በመሆኑ ገመናቸውን አውጥቶ የማሳየት አቅሙ ከፍ ያለ ነው።ገፀባህሪያቱን በሙሉ ከመነሻቸው እስከ መዳረሻቸው ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ መልካቸውን የተገነዘበ በመሆኑ በአእምሮአቸው የሚመላለሰውን ሆነ ያለባቸውን ችግር እንዱሁም ችግራቸውን ለማስወገድ የሚያደርጉትን ጥረት ለአንባቢን ያሳውቃል።ስለ ገፀ ባህሪያቱ ድብቅ ሚስጥርም ሆነ ውስጣዊ ስሜት እንዲሁም ስለ ገጠማቸው ችግር የተከታተለ በስፋት ስለሚተርክ በአንባቢውና በእነሱ መካከል እንዲኖር የሚፈለገውን ኪነ-ጥበባዊ ቅርበት ያጎላዋሌ።"(ዘሪሁን አስፋው 2005፣191)

## 2.2.6.2 ውስን ሁሉን አወቅ አንፃር

ከስሙ እንደምንረዳው ይህ የአተራረክ ዘዴ እንደ ሁሉን አወቅ አንፃር ሶስተኛ መደብ ቢሆንም በተለያየ መልኩ የሚገደብና የሚወሰን ነው። ዘሪሁን አስፋው "የሰነ ፅሁፍ መሠረታውያን" በሚለው መፅሀፉ ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ እንድህ ሲል ገልፆታል፡-

> ደራሲው በአንድ ዋነኛ ገፀባህሪ ጥላ ስር ሆኖ በታሪኩ ስጥ የሚፈጠሩ ሁነቶችን እና ክዋኔዎችን ከገፀባህሪው እይታ ወይም አስተሳሰብ አንፃር ያቀርባል። ለዚህም ገፀባህሪ ይበልጥ ቅርበት ያላቸው ገፀባህሪያት በውል ሲታወቅ ሌሎቹን ለማወቅ አዳጋች ይሆናል። ውስን ሁለን አወቅ አንፃር ገፀባህሪያትን ከአንባቢ ጋር በማቀራረብ ረገድ ከሁለን አወቅ አንፃር የተሻለ ነው። የሚያስከትለው ችግር የተመረጠው ገፀባህሪ የሚያቀርበውን ከመከታተል አንባቢው አልፎ ስለማይሄድ እና የገፀ ባህሪውም እውቀት የተመጠነ ሊሆን ስለሚችል አንዳንዴ አስፈላጊ ነገሮችን አንባቢው ሊያጣ ይችላል። አማርኛ ልብ ወለዶች ብዙዎቹ በዚህ አንፃር የተተረኩ ናቸው።(ዘሪሁን አስፊው፣2005፣194 )

## 2.2.6.3 አንደኛ መደብ አንፃር

ይህ የአተራረክ አይነት ደራሲው በልብ ወለዱ ገፀ ባህሪያቶችን ገላጭ አድርጎ ስለታሪኩ፤ ስለተለያዩ ክስተቶች፤ ስለገፀ ባህሪያቶች እንዲሁም አጠቃላይ ልብ ወለዱን እንዲተርኩ የሚያደርግበት የአተራረክ ዘዴ ነው። ይህን ዘሪሁን አስፋው "የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን እና አተገባበር" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ ሲል ገልፆታል።

> ተራኪው ‹‹እኔ›› ይህን አየሁ ይህን ተመለከትኩ እገሌ የሚባለው ገፀባህሪ በዚህ ወጣ በዚያ ወረደ እገሌ ደግሞ እንዲህ ያለ ችግር ደረሰበት እገሌ እና እገሌ ተፋቀሩ፣ተጣሉ ወይም በራሴ ላይ እንዲህ ያለ ድርጊት ተፈፀመብኝ። እንትናን ወደድኩ፣ ጠላሁ ወ.ዘ.ተ እያለ የሚተርክበት የአንፃር አይነት ነው። ተራኪው በታሪኩ ውስጥ ተሳትፎ ወይም ታሪኩን በቅርብ የተከታተለ በመሆኑ ከሞላ ጎደል እንዳለ ያቀርበዋል ተብሎ ስለሚታመን በዚህ አንፃር የሚተረከው ታሪክ እውነታዊ ምትሀቱ ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል።( ዘሪሁን አስፋው፤ 2005፤ 197)

## 2..2.6.3 ተውኔታዊ አንፃር

ይህ የአተራረክ አይነት ከላይ ከሰፈሩት ከሶስቱም የአተራረክ አይነቶች የተለየ ነው። ተውኔታዊ አንፃር ለቴአትር ፅሁፎች ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን በዚህ የአፃፃፍ ዘዴ አንባቢያን ሙሉ ታሪኩንና ሂደቶቹን ከገፀ ባህሪያቶች ቃለ ምልልስ፤ ገላፃዎች፤ እርስ በእርሳቸው ባላቸው መስተጋብር፤ እንዲሁም በድርጊቶቻቸው አጠቃላይ ድርሰቱን የሚረዱበት የአተራረክ ዘዴ ነው። ዘሪሁን አስፋው ተውኔታዊ አንፃርን "የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን እና አተገባበር" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ ሲል ገልፆታል።

> ተውኔታዊ አንጻር ተራኪው በገጸባህሪያቱ ድርጊትም ሆነ በሁኔታዎች አይነት አስተያየት የማይሰጥበት የአንጻር አይነት ነው። ገጸባህሪያቱ የሚናገሩትን ወይም ያዳምጣል፣ ያስተውላል። ከዚያም ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ችግራቸውን ወይም የሚያሳስባቸውን ጉዳዮች ይገነዘባል።

አንባቢው በመድረኩ ላይ የቀረቡ ተዋንያንን እንዲመለከት ነው። (ዘሪሁን አስፋው 2005፤ 200)

## 2.2.7 ትልም

ትልም የልብ ወለዱ ታሪክ በቅደም ተከተል፤ በምክንያትና በውጤት እየተሳሰሩ ድርጊቶችን የሚይዝልን የልብ ወለድ ወሳኝ አላባዊ ነው። እያንዳንዱ ክስተቶች ወይም ደሞ ሁነቶች በታሪክ በኩል ይተረካሉ። ነገር ግን ትልም እያንዳንዱን የታሪኩ ፍሰት ውስጥ ያሉ ድርጊቶችን ለምን እደተደረጉ ያስረዳል። ስለ ትልም ዘሪሁን አስፋው "የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን እና አተገባበር" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ ሲል ገልፆታል።

> ትልም ማለት በአንድ ልብ ወለድ ውስጥ ምን? ለምን ተደረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘውን መልስ የሚያካትት ወይም ደግሞ በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈፀሙ ሁነቶችን የተደረገበት ምክንያትና የሚያስከትሉትን ውጤት ጥብቅ ቁርኝነት የያዘ የልብ ወለድ አካል ነው (ዘሪሁን አስፋው፤ 2005፤ 158)

## 2.3 የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ በ2016 በአመዩ ነ ገ ራ ለባችለር ኦፍ አርትስ የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ "ቤባንያ" ልብ ወለድ ከረጅም ልብ ወለድ አላባዊያን አንፃር ትንተና በሚል ርዕስ ከአላባውያን አንፃር ትንተና አድርጓል። ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች ያላቸው ተመሳሳይነት ሁለቱም ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ አላባውያን አንፃር መተንተናቸው እና ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች በአራት ምዕራፎች መከፋፈላቸው ተመሳሳይነት አላቸው። ልዩነታቸው ደግሞ የሁለቱም ልቦለዶች ልዩነት እንዳለ ሆኖ አጥኝው ተጨማሪ የልቦለዱን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በራሳቸው ተንትነዋል።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1 የመረጃ ትንተና

### 3.1.1 ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ታሪክ በአጭሩ

ታሪኩ የሚጀምረው ተራኪው በመንፈስ ተጉዞ ሲጨነቅ ነው። በመንፈስ ተጉዞ በሚጨነቅበት ጊዜ ከዚህ ጭንቀት የሚገላግሉት ካህኑ ዮቶር እንደሆኑ በመገንዘብ እርሳቸውን ለማግኘት አብዝቶ ይፀልያል። ከዚህ ጭንቀት ወይም የአይምሮ መረበሽ በሚነቃበት ጊዜ እራሱን ኢሪዱ ወዴተባ አለም ያገኛል። ወደዚህ አለም ያመጡትም አንድ ሽማግሌ እንደሆኑ ሲነቃ አጠገቡ ያገኛት ኪራ የተባለችው ሴት ትነግረዋለች። እናም ኢሪዱ እራሱ ከሚኖርበት አለም ጋር አብራ የተሰራች ብትሆንም የተለየች መሆኗን ትገልፅለታለች። ኪራ ተራኪውን ወደዚህ አለም የመጣው ለሆነ አላማ ተልኮ እንደሆነ እርግጠኛ ሆና ትነግረዋለች። ተራኪውም በንግግሯ እና ባለበት አለም ውስጥ ግራ ሲጋባ ቆይቶ ያመጡትን ሽማግሌ ማግኘት እንደሚፈልግ ይነግራታል። ተራኪውም በዚያ የአዕምሮ መረበሽ ውስጥ ሆኖ ሳለ የእሱ ኮብላይ ካህኑ ዮቶር መሆኑን ያ ድምፅ የእርሳቸው መሆኑን ተገነዘበ። ኪራም ሽማግሌውን በሩን እንዳለፈ እንደሚያገኘው ተናግራ መፅሀፍ ፊቷ ላይ አስቀምጣ ስለ ኢሪዱ ታሪክ ታጫውተዋለች።

ተራኪው ህልሙን ለማሳካትና ጥበብን ለመሸመት የሚወዳቸውን ቤተሰቦቹን ትቶ ፍርሀቱን አሸንፎ ጉዞውን ይጀምራል። የሚያስጨንቀውን መንፈስ ማህበረሰቡ ሀኪሞችም ሳይቀሩ የአዕምሮ ህመም ነው ብለውታል። ህኪም እና ፀበል ሞክሮት ሊሻለው ግን አልቻለም። የጀማመረው ከሲጳራ የተረከበው የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት እንዲዘጋ ከተደረገ ጀምሮ ነው። ይህ ድርጅት ከተዘጋ በኋላ የሲጳራን አደራ በላሁ በማለት እራሱን ጭንቀት ውስጥ ከቶ ነበር። ለዚህ የአዕምሮ መረበሽ ያበቃውን ምክንያት ነው ብሎ ቢደረድርም በቂ ሆኖ ግን አያገኘውም። ይህን ጭንቀት የተረዳችው ባለቤቱ እንቁጣጣሽ በመንፈሱ ጠንካራ እንድሆንላት እና ከሌሎች የተለየ ችሎታ እንዳለው በመናገር ህልሙን እንዲያሳካና ፍርሀቱንም እንዲያስወግድ መንፈሱ ጠንካራ እንዲሆን ታበረታታዋለች። ተራኪውም በመጀመሪያ ሀጂ በተደጋጋሚ በህልሙ ስለታዩት ወዴ ሐጂ ቤት ያቀናል። ከሐጂ ጋርም ተገናኝተው የሆነውን ሁሉ ይነግራቸዋል። ሐጂም የሚሆነው ሁሉ በምክንያት ነው ብለው ማበረታቺያ እንዲሆነው ምሳሌ ጠቅሰው ሲጨዋወቱ ያመሻሉ።

ተራኪው ሐጂ ላይ ሰንብቶ ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ በአውቶብስ ገብቶ በሚጓዝበት ጊዜ ላይላ የተባለች ወጣት ታማ በጩኸት ተዝለፍልፋ ትወድቃለች። ተራኪው አውቶብሱን አስቁሞ በአካባቢው ወደሚገኝበት ጤና ጣቢያ ይዟት ይሄዳል። ላይላ አመሻሹ ላይ ትነቃለች። ተራኪው ስላደረገላት ነገር ሁሉ ታመሰግነዋለች። በነጋታው ሀኪሞቹ መውጣት እንደምትችል ይነግሯታል። ቁርሳቸውን እና ምሳቸውንም አቶ ዳባ የተባለ የሀኪም ቤቱ ጥበቃ ይሰጣቸዋል። ከሀኪም ቤቱ ወጥተው ወዴ ከተማ የሚወስዳቸው መኪና ወደሚገኝበት ቦታ ይሄዳሉ። መኪና ሲያጡ የመሸበት

ብለን እናድራለን ብለው ትንሽ ተጉዘው አንዲት ዛፍ ስር እንደተቀመጡ ትንሹ ዮቶር ከብት እየነዳ፣ ዋሽንት እየነፋ መጥቶ ወዴ ቤታቸው ይወስዳቸዋል። ተራኪው ዮቶር ብሎ ማን እንዳወጣለት ሲጠይቀው የኔታ ራጉየል ናቸው ብሎ ይነግረዋል። ተራኪውም እነዚህ ሰው የኔ ኮብላይ ካህኑ ዮቶር ናቸው ብሎ ተገነዘበ። የትንሹ ዮቶር አባት ጋሽ ንጉሴ አሉ የተባሉ የሰፈሩ አስታራቂ እና ብልህ አስተዳዳሪ ናቸው። እነ ላይላን እንደቤተሰብ ተቀብለው አስተናገዷቸው። አንድ ቀን ማታ ላይላ ያሳለፈችውን የስቃይ ጊዜ ለተራኪው ትነግረዋለች። ሁለት ባል አግብታ ሁለቱንም በሞት ስለተነጠቀች በአካባቢው ማህበረሰብ የደረሰባትን የስቃይ ጊዜያቶች አንድም ሳይቀር ትነግረዋለች። ተራኪውም በጣም ታሳዝነዋለች። እነ ጋሽ ንጉስ ቤት ለጥቂት ቀናት ከቆዩ በኋላ የኔታ ራጉኤል ይገኙበታል ወዴተባለችው ሌጣ አዛዥ ከተማ ጋሽ ንጉስ ታመን ከተባለ እቃ አመላላሽ ጋር ይሸኟቸዋል። ከተማ ሲደርሱ የሐጂ ተማሪ ከሆነው ከያቆብ አይናማው እና ከካህኑ ዮቶር ጋር ጋር ይገናኛሉ። ሁሉም በደስታ ይፍለቀለቃሉ። ካህኑ ዮቶር ፍርሀታቸውን አስወግደው ወደተጠሩበት አለም በመምጣታቸው ተደስተው ይህም አንዱ የስኬት ደረጃ መድረሳቸውን የመጡበትን አላማ ትውልዱ ማንቃት ለጥበብ እንዲተጋ ማድረግ መሆኑን ይነግሯቸዋል። መፅሀፈ ዳጉን ብዙ ሚስጢራቶችን የያዘ በመሆኑ እነዚህን ሚስጢር የሚያውቅ እና የሚፈታ ትውልድ ሰለሚያስፈልግ ትውልዱን እናንቃ መፅሀፉ ትውልዱ ፈቶ የማይጨርሰው ሚስጢር መያዙን ይነግሯቸዋል። ተራኪውም ከዮቶር ብዙ ትምህርቶችን ይቀስማል። ለሌላው የማይታየው ሚስጢር ለእርሱ ይታየዋል። ተራኪው ብዙ ጥበብ ሸምቶ ቤተሰቡ ጋር ሊሄድ መሆኑን ሲያስብ በጣም ይደሰታል።

ከኮብላዩ ካህን ጋር ላይላና  ያቆብ አይናማው ሆነውተያይዘው ትንሹ ዮቶር ወዳለበት ቦታ ተመልሰው መጥተው ለሶስት ቀናት እዚያ ያሳልፋሉ። ከሶስት ቀን በኋላ ተራኪው ወደ ባለቤቱ እንቁጣጣሽ እና ልጆቹ ሊመለስ ነው። ላይላ እና ያቆብ አይናማው ደግሞ ይፋቀራሉ።

## 3.1.2 ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር ትንተና

### 3.1.2.1 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ከ ታሪክ አንፃር ትንተና

የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ታሪክ በምዕራፍ ሁለት ለማየት እንደተሞከረው ደራሲው በሰጠው ጊዜ እና ቦታ በቅደም ተከተል መሰረት የታሪኩን ቁርኝት ይተርካል። የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ታሪክ መጀመሪያ፣ መሀከል እና መጨረሻ ያለው አንዱ ላንዱ የተሳሰረ ሰንሰለት ያለው እስኪመስል ድረስ በፅናት የተሳሰረ ነው። ታሪኩ በገፀ ባህሪያቶቹ ላይ አንዳቸው ለአንዳቸው ያላቸው ፍቅር እና መተሳሰብ በሌላ በኩል ደግሞ የመፅሀፈ ዳጉን ፈላጊዎችን ክፋት፣ የእምነትን ፍቅር እና ለዳጉን መፅሀፍ የከፈለችውን ዋጋ፣ የእንቁጣጣሽ ባለቤት አላማው ላይ ለመድረስ ያለውን ፅናት እና የዮቶር ትንሹን ጥበብ ያሳያል። ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ከእነ እንቁጣጣሽ ቤት እስከ ኢርዱ የሚባል ሌላ አለም ከኢርዱ እስከ ከኢርዱ እስከ ሌጣ አዛዥ ከሌጣ አዛዥ እስከ እነ ትንሹ ዮቶር ቤት ከእነ ትንሹ ዮቶር እስከ የኔታ ራጉኤል ያሉበት ቦታ ድረስ በምናብ የሚያስጉዘን ሲሆን ፊደል ለመፅሀፈ ዳጉን ብሎ የሚወዳትን ፍቅረኛው በእምነት በጠላት እጅ ሆና በምትሰቃይበት ጊዜ ለመጭው ትውልድ

ብሎ በመፅሀፉ ሳይለውጣት መቅረቱን፣ ከጠላቶቹ ለማምለጥም ህይወት በልዩ ልዩ መንገድ ያጋጠመችበትን ችግር ወይም ፈተና ለማሸነፍ ገፀ ባህሪው ሲፍጨረጨር ያሳየናል። ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ታሪክ አንድ ታሪክ ማሟላት ያለበትን የነገሮች ቅደም ተከተል በገፀ ባህሪያት የሚፈፀሙትን ድርጊቶች አነሳስ፣ አፈፃፀም እና የመጨረሻ ውጤት ለአንባቢያን አድርሷል።

### 3.1.2.2 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ የገፀ ባህሪያት አሳሳል

በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ እንደተሞከረው የገፀ ባህሪ አሳሳል ማለት ደራሲው የፈጠረውን ታሪክ ተሸክመውልን የሚጓዙና እንደ ታሪኩ የየራሳቸው የአሳሳል ጥበብ ያረፈባቸው አካላት ናቸው። ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ሶስት ዋና ዋና ገፀ ባህሪያት ሲኖሩት ስድስት አስተኔ ገፀ ባህሪያትን ያካተተ ነው።

#### 3.1.2.2.1 የላይላ አካላዊ አሳሳል

የላይላን አካላዊ አሳሳል ስንመለከት እድሜዋ በ20ዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝ መልከ መልካም ወጣት ናት። ለዚህም እንደ ማጣቀሻነት ከመፅሀፉ ወስደን እንመለከታለን።

"ጠዋት እንዳጫወተችኝ ከሆነ የሀያ አምስት አመት ወጣት ናት።"/ገፅ፣ 47/

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ላይላ በሀያዎቹ የእድሜ ክልል እንደምትገኝ ነው።

#### 3.1.2.2.2 የላይላ ማህበራዊ አሳሳል

የላይላ ማህበራዊ አሳሳል ስንመለከት ሀይማኖቷ ሙስሊም ስትሆን በወጣትነቷ ሁለት ባሎችን አግብታ ሁለቱንም በሞት በመነጠቋ ምክንያት በማህበረሰቡ ተወግዛ የትውልድ ቦታዋን ለቃ ተሰዳ ሌላ ከተማ ውስጥ ቡና ቤት በመሸጥ እራሷን ታስተዳድር የነበረች ወጣት ናት። ይህን እንደማስረጃነት ስንጠቀስ፦

"በዚህ እድሜዋ ሁለት ጊዜ አግብታለች፤ ሁለቱም ትዳሮቿ ግን በባሎቿ ሞት ተደምድመዋል። በምትኖርበት ማህበረሰብ እና በባሏ ቤተሰቦች መተተኛ፣ ጠንቋይ፣ ገፊ ተብላ ተደብድባለች፣ ተወግራለች፣ የሰውነት ክብሯን አጥታለች።"/ገፅ፣47/

"አንድ አምስት ወር እንደሰራሁ ደግሞ፥ የቡና ቤቱ ማናጀርም ገላዬን ተመኝቶ ስቃየን ያሳየኝ ያዘ። ፈቃዱን ብፈፅምለት የሚፈጠረውን ችግር ከሌሎቹ ሴቶች ልምድ አውቀዋለሁ።"/ገፅ፡ 84/

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ላይላ በዚህ የእድሜ ክልል ሆና ሁለት ባል አግብታ እንደነበር እና ሁለቱንም ባሎቿን በሞት በመነጠቋ በአካባቢው ማህበረሰብ ተወግዛ እንደነበር ይገልፃል። በተጨማሪም ለብዙ ወራቶች ቡና በመሸጥ ትተዳደር እንደነበረ ያሳየናል።

በአዕምሮ ህመም ምክንያ ከምትወደው ትምህርት አቋርጣለች፤ የቤት ሰራተኛ ሆና በምትሰራበት ወቅት በቤት አባወራው ተደፍራ አርግዛ የነበረ ስሆን ልጁንም ለመውለድ ሀቅም ስላልነበራት ለማስወረድ ተገዳለች።

### 3.1.2.2.3 የላይላ ሞራላዊ አሳሳል

ላይላ ከሞራላዊ አሳሳል ደረጃ ስንመለከታት ጥሩ ሰነ ምግባር ያላት፣ ከሰው ጋር ቶሎ ለመግባባት የምትሞክር እና ከሁሉም የበለጠ የእይታ ጥበብ የተሰጣት ጥሩ ስነ ምግባር ያላት ወጣት ናት። ላይላ ምንም አይነት ስግብግብነት የሌለባት ብሩህ አዕምሮ የተካነች ናት። ይህንንም እንደ ማጣቀሻነት ወስደን እንመለከታለን።

"አንድ ሰው መላእክቱን በዋሽንት እያዋራቸው ነው። መላእክቱም በዚህ ዝማሬ እንደኔ የተደሰቱ ይመስለኛል። እየሰማኸው ነው ግን" አለችኝ

"ከዛፎቹ ሿሿታና ከሚያፏጨው ንፋስ ውጭ ምንም የሚሰማኝ ነገር አልነበረም።"/ገፅ፣ 51/

ይህ ማለት ላይላ እና ተራኪው ተቀምጠው በሚያወሩበት ጊዜ ላይላ ተመስጣ የዋሽንት ድምፅ በምትሰማበት ጊዜ ተራኪው ግን ከንፋስ ድምፅ ውጭ ምንም ድምፅ አይሰማውም። ይህ ማለት ላይላ ከሌሎች ሰዎች የተለዬ ጥበብ የተሰጣት መሆኑን ያሳየናል።

### 3.1.2.2.4 የላይላ ስነ ልቦናዊ አሳሳል

ላይላ ከስነ ልቦናዊ አሳሳል አንፃር ስንመለከታት  ደግ እና አዛኝ ልብ ያላት፣ ሩህሩህ፣ ተግባቢ፣ ሰውን ወዳድ እና በወጣትነት እድሜዋ ያሳለፈቻቸውን የመከራ እና የችግር ሰቃዮችን ባስታወሰች ቁጥር እንባዋን መቆጣጠር እሰኪያቅታት ድረስ ክፉኛ የምትግዳ ወጣት ናት።

"የጠየኩት አንድ ነገር ብቻ ነው፤ 'በቅቶኛል፣ ደክሞኛልና ልሂድ' ነው ያልኩት። ወደማይቀርበት አለም። እርሱንም ሞከርኩ፤ እምቢ አለኝ። አላህ አልፈቅድ አለ። ምን ፈልጎ ይሆን ከኔ?... ግራ ገብቶኛል።"/ገፅ: 48/

ከዚህ እንደምንረዳው ማህበረሰቡ ላይላ ላይ ባደረሰባት የስነ ልቦና ጉዳት ህይወቷን እስክትጠላ ድረስ በስነ ልቦና ተጎድታ እንደነበር ያሳያል።

### 3.1.2.2.5 የኔታ ራጉየል አካላዊ አሳሳል

እድሜያቸው በግልጽ ባይታወቅም ከ50 በላይ  ይደርሳል ብሎ ለመናገር ያስደፍራል። መልከ ቀና እዲሁም መካከለኛ ቁመት እዳላቸዉ ይነገራል። የኔታ ራጉኤል የቤተ ክህነት አስተማሪ እደመሆናቸዉ መጠን የሚለብሱት ከሸማ የተሰራ እጀ ጠባብ ፣ተነፋነፍ ሱሪ እንዲሁም ካባ ደርበዉ ነጭ ጥምጣም ይጠመጥማሉ።

### 3.1.2.2.6 የኔታ ራጉኤል ማህበራዊ አሳሳል

የኔታ ራጉኤል ከማህበራዊ አሳሳል አንፃር ስንመለከታቸው በቤተክርሰቲያን አስተምሮ የበቁ ሁሉን በሚገባ የጨረሱ እንዲሁም የመፅሀፈ ዳጉንን ሚስጥር ከሌላው ማህበረሰብ በበለጠ የሚያውቁ ናቸው። የኔታ ራጉኤል በቤተ ክህነት አስተምሮ በብዙ ቦታዎች እየተዘዋወሩ ብዙ ተማሪዎችን የቤተ ክህነትን ትምህርት ያስተማሩ እጅግ ብልህ የጥበብ ሰዉ መሆናቸውን ያሳያል። ይህንን እንደማጣቀሻነት ከመፅሀፉ ወስደን እንመለከታለን።

"ብዙ ጊዜ መሔዳቸውን እንጂ ወዴት እንደሚሄዱ የመናገር ልምድ የላቸውም፤ በየስፍራው የሚያስተምሯቸው ልጆች አሏቸው፤ አልፎ አልፎ እንዳንተ ያሉ ወጣቶች እየመጡ ይጎበኟቸዋል። ሄድ መለስ እያሉ ነው የሚኖሩት፤ ቢሆንም የሄዱበትን ማወቁ ይቸግራል ብዬ አላስብም። ነገ እናጠያይቃለና!" አሉኝና ፋታ ወስደው ቀጠሉ…

"የኔታ የጥበብ ጎተራ ናቸው፤ አጭደው የማይጨርሱት የጥበብ አዝመራ።"/ገፅ: 62/

ከዚህ የምንረዳው የኔታ ራጉኤል በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩ ጥበብን ያስተምሩ እንደነበርና በትምህርታቸውም የተካኑ አባት መሆናቸውን ያሳየናል።

### 3.1.2.2.7 የኔታ ራጉኤል ሞራላዊ አሳሳል

የኔታ ራጉኤል ሞራላዊ አሳሳል ሁኔታ ስንመለከት ያወቁትን ጥበብ ለተማሪዎቻቸው እና ለማንኛውም የጥበብ ፈላጊ ትግስት እና ትህትና በተሞላበት መልኩ ለማሳወቅ የሚፈልጉ የጥበብ ሰው ናቸው። እራሳቸውን ዝቅ አድርገው ትህትናን የሚሰብኩ እና ሰነፎችንም እንዲጠነክሩ ለማስተካከል የሚሹ ናቸው። ከእውቅና እና ስልጣን በፊት እውቀት እንዲቀድም ይመኛሉ፣ ያለቦታዉ፣ ያለችሎታዉ፣ ያለዕውቀቱ የሚገኑትን ሰዎች ጠንክረው ተምረው የተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ የሚመክሩ አባት ናቸው።

"የኔታ የጥበብ ጎተራ ናቸው፤ አጭደው የማይጨርሱት የጥበብ አዝመራ ያገኙትን ሰው በሙሉ በጥበብ ሳይኩሉ አያልፉም።"/ገፅ፣ 62/

ከዚህ የምንረዳው የኔታ ራጉኤል እርሳቸው የሚያውቁትን ጥበብ ለሌሎች የሚያስተምሩ ስግብግብነት የሌለባቸው መልካም አባት መሆናቸውን ይገልፅልናል።

### 3.1.2.2.8 የኔታ ራጉኤል ስነ ልቦናዊ አሳሳል

የኔታ ራጉኤል ስነልቦናዊ አሳሳላቸው ስንመለከት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የቤተ ክህነትን ትምህርት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የሚያስተምሩ የዋህና ግልፅ ናቸው። ወጣቶች አዕምሯቸውን ለጥበብ ክፍት

አድርገው ፍርሀታቸውን ወዴ ጎን በመተው እራሳቸውን ለአድስ ነገር እንዲያዘጋጁ በሰነ ልቦናቸው ጠንካራ እንዲሆኑ ይመክራሉ። ይህንን እንደማስረጃነት እንመልከት።

"በምስጋና ትጋ፤ ከህይወት ታረቅ፤ ለራስህም ሆነ ለሌሎች ይቅርታ በማድረግ በይቅርታ ፀበል ራስክን አንፃ። እርግማንህን ስበር። እስከዛሬ ራስክም ላይ ሆነ ሌሎች ላይ ላወረድካቸው የእርግማን ቃላት ንስሀ ግባ።"/ገፅ፣ 186/

ከዚህ እንደምንረዳው የኔታ ራጉኤል ወጣቶች ወደፊት ለሚገጥሟቸው ፈተናዎችን ለማለፍ በሰነ ልቦና ተዘጋጅተው እንድጠብቁና ፈተናዎቻቸውን ድል የሚያደርጉበት መንገዶችን እየገለፁላቸው መሆኑን ያስረዳናል።

## 3.1.2.2.9 ዮቶር ትንሹ አካላዊ አሳሳል

የዮቶር ትንሹ አካላዊ አሳሳል ስንመለከተው እድሜው የአስር አመት አካባቢ የደረሰ ህ ፃ ን ሲሆን መልከ መልካም ከእጁ ዋሽንት የማይለይ ህፃን ነው። ይህን እንደማስረጃነት ስንጠቅስ፡-

"የከብቶች ድምፅ ከወዲያ ማዶ እየተሰማን ቆየና ካለንበት ደረሱ፤ ከኋላቸው እድሜው አስር ዓመት አካባቢ የሆነ ትንሽ ልጅ ወደ እኛ እየተመለከተ ይራመዳል፤ ዋሽንት ይዟል።"(ገፅ፣52)

ከዚህ እንደምንረዳው ትንሹ ዮቶር እድሜው አስር አመት አካባቢ ሲሆን ዋሽንት ከእጁ እንደማይለይ ይገልፅልናል።

## 3.1.2.2.10 ዮቶር ትንሹ ማህበራዊ አሳሳል

ዮቶር ትንሹን ከማህበራዊ አሳሳል ስንመለከተው የጋሽ ንጉሴ የመጀመሪያ ልጅ እና የየኔታ ራጉኤል ተማሪ ነው። ስሙንም ዮቶር ብለው ያወጡለት የኔታ ራጉኤል ናቸው። ይህን እንደማስረጃነት ስንመለከት፡-

"ስምህ ግን ማነው ማሙሽ?

"እናቴ ያወጣችልኝ ታምሩ ብላ ነበር። ኋላ ግን የኔታ አባቴን 'ዮቶር በለው' አሉትና ዮቶር አለኝ"

ይህ ማለት ዮቶር ብለው ያወጡለት የኔታ ራጉኤል እንደሆኑ ይገልፅልናል።

ትንሹ ዮቶር ከአካባቢው ህፃናት የተለየ የእይታ ጥበብ ስላለው እና የተረዳውን ነገር ለጓደኞቹ ሲነግራቸው ስለማይቀበሉት በጓደኞቹ ላይ ብዙም ተሰሚነት የለውም።

## 3.1.2.2.11 ዮቶር ትንሹ ሞራላዊ አሳሳል

ዮቶር ትንሹ ሞራላዊ አሳሳሉ እናት እና አባቱን አክባሪ፣ ታዛዥ እና ትህትናን የተላበሰ ህፃን ነው። ዮቶር ትንሹ ጥበብን በገንዘብ መለወጥ የማይፈልግ አስተሳሰቡ ሁሉ እንደ ህፃን ሳይሆን እንደ አዛውንት መሆኑን ያሳየናል።

### 3.1.2.2.12 ዮቶር ትንሹ ስነ ልቦናዊ አሳሳል

ትንሹ ዮቶር ስነ ልቦናዊ አሳሳሉን ስንመለከተው የስነ ልቦናው ጥንካሬ እና ነገሮችን የሚረዳበት መንገድ እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ህፃን ነው። ዋሽንት አብዝቶ ስለሚወድ ሁልጊዜ ከብት እየጠበቀ ብቻውን ሆኖ ዋሽንት በሚጫወትበት ጊዜ ተፈጥሮ ሁሉ እሱን ተከትላ ያዜሞች እስኪመስለው ድረስ ተመስጦ ዋሽንቱን ሁልጊዜ ይጫወታል።

### 3.1.2.3 ዮቶር 2 ረጅም ልበለድ ትልም

ትልም በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀው ልበለዱ ውስጥ ምን? ለምን? ተደረገ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘውን መልስ የሚያካትት ነው። ዮቶር 2 ረጅም ልበለድ በምክንያት እና በውጤት ዙሪያ ተመርኩዞ የሚያጠነጥን ነው። ለዚህም እንደማስረጃነት ፊደል እና አቤሜሊክ ያደረጉትን ንግግር እንመለከታለን።

"እሽ አባቴ። ግን ፈረሴ ላይ ልጫንዎትና ቢያንስ መንደር እንኳን ላድርሶት። ከዚያ እንዳሉኝ አደርጋለሁ። መድሀኒት..."

"ጊዜ የለም!" አቋረጡት። ደግሞም የወደቀውን የአቤሜሊክን አካል እዚሁ ተወው። ቀሪው ጉዞህ ያን የብቻህ ነው። እኔ በሔድክበት መንገድ ኹሉ በመንፈስ እከተልሀለሁ።"

"ተደናግሮ እና ተደናግጦ ድምፅ ማውጣት እንዳቃተው የካህኑ እጅ፥ እጁ ላይ ሲሟሟ ታወቀው። ድንገትም ትንፋሻቸው ጸጥ አለ። የአዳኞቻቸው ርኩስ መንፈስ ቀድሞም ተሰምቶታል፤ እናም የአይኖቻቸውን ቆቦች ከድኖ፣ አጭር ፀሎት አልጎምጉሞ፣ ከተቀበለው አደራ ጋር ዘ'ሎ ፈረሱ ላይ ወጥቶ ሽምጥ ጋለበ።"/ገፅ፡ 15/

ከዚህ እንደምንረዳው ካህኑ አቤሜሊክ መፅሀፈ ዳጉንን ከጠላቶቻቸው ለማሸሽ በሚሰደዱበት ወቅት ደክሟቸው ስለነበረ መፅሀፉን የሚወስድ ጠንካራ ሰው እንዲልክላቸው አምላካቸውን እየለመኑ ሳለ በከፍተኛ ማዕበል ፊደል ደርሶ መፅሀፉን ከአቤሜሊክ ተቀብሎ ከጠላቶቹ ለማምለጥ በፈረስ ጋልቦ ይሰወራል። ጠላቶቹም መፅሀፉን ባለማግኘታቸው ምክንያት በርካታ ንፁሃንን እያሰሩ በግፍ ሲያሰቃዩዋቸው እና ሲገድሏቸው ነበር። ይህ መፅሀፍ ፊደል የሚወዳትን ፍቅረኛውን በእምነትን እንዲያጣት ምክንያት ሆኖታል። ትልም በምክንያት እና በውጤት የተመሰረተ ስለሆነ ዮቶር 2 ረጅም ልበለድ ምን? ለምን ተደረገ? ከዚያስ ምን ውጤት አገኘ? የሚለውን ይገልፅልናል። ዮቶር 2 ረጅም ልበለድ መግቢያ፣ መሀከል እና መጨረሻ ያለው ልበለድ ሲሆን በመጀመሪያ የገፀ

ባህሪያቶችን ማንነትና ፍላጎት በጥልቀት ባይሆንም ለማሳየት ሞክሯል፤ በመካከል ላይ ገፀ ባህሪያቶች አላማቸው ላይ ለመድረስ ያላቸውን ፅናት እና በመጨረሻም የእንቁጣጣሽ ባለቤት ያሰበው ሁሉ ተሳክቶለት ወደ ቤተሰቡ ሊመለስ መሆኑን እና ላይላ ከያቆብ አይናማው ጋር የፍቅር ግንኙነት ጀምራ ፍፃሜያቸው እንደፈለጉት ሆነላቸው። ይህም አንድ ልቦለድ ማሟላት ያለበትን ትልም ዮቶር 2 አሟልቷል።

## 3.1.2.4 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ መቼት

መቼት ልቦለዱ የሚከናወንበት ጊዜ እና ቦታ ነው። የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ የጊዜ መቼት ከ1928 አሁን እስካለንበት ሲሆን ታሪኩ የተፈፀመበት ቦታ አጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ዉስን መቼት በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ እንደተሞከረው በአጠቃላይ መቼት ስር ሆኖ ታሪኩ የተፈፀመበት ውስን የቦታ እና ውስን የጊዜ መቼት ሲሆን የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ውስን መቼትን ለማስረዳት ከመፅሀፉ ተቅሰን እንመለከታለን።

"በነገራችን ላይ ከተማ የሚያደርሰን መኪና ባይገኝ እንኳ እዚህ ተፈጥሮ ውስጥ ባድር ምንም አይመስለኝም።" አለችኝ

"ካልተገኘ እዚህ እኮ እንደ ከተማ አይደለም፤ ከአንዱ ጎጆ ሄደን 'የመሸበት መንገደኛ ነን፤ አሳድሩን' እንላለን አይዞሽ!" አልኳት።

"ትንሽ እንደተጓዝን "እዚያች ዛፍ ስር አረፍ እንበል።" ብላኝ ወደ ዛፏ አመራች። ተከተልኳትና ጎኗ ቁጭ አልኩ።"/ገፅ፡ 50/

ላይላ እና የእንቁጣጣሽ ባለቤት በአንድ ገፀር አካባቢ ወዴ ከተማ ለመግባት በሚጓዙበት ወቅት ደክሟቸው አንዲት ዛፍ ስር ይቀመጣሉ፤ ይህም አንዱ የልቦለዱ ውስን ቦታ ሲሆን ሰዓቱም ማታ ጊዜ አመሻሽ ላይ ነው።

የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ውስን መቼቶች "የእነ ጋሽ ንጉስ ቤት" ላይላ እና የእንቁጣጣሽ ባል መሸቶባቸው የእግዜር እንግዳ ብለው ያደሩበት ቤት ነው፤ ሁለቱ ዛፍ ቆራጮች በአካባቢው ማህበረሰብ እርቅ የተከናወነበት ጫካ ቦታ፣ "በረንዳ" ላይላ ተቀጥራ ቡና የምትሸጥበት ውስን ቦታ ነው፣ ሌጣ አዛዥ ከተማ ውስጥ እነ ላይላ ያረፉበት ሆቴል፣ የየኔታ ራጉኤል ቤት፣ "ሀኪም ቤት" ላይላ በአውቶብስ ተሳፍራ በምትጓዝበት ወቅት ለህክምና የሄደችበት ውስን ቦታ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ልቦለዱ የተከናወነበት ውስን ቦታዎች ናቸው።

## 3.1.2.5 የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ግጭት

በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ እንደተሞከረው ግጭት በሰዎች ወይም በገፀ ባህሪያቶች አለመግባባት የሚደረግ ፍልሚያ ነው። ሶስቱን የግጭት አይነቶችን በዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ በማጣቀስ እንመለከታለን።

### 3.1.2.5.1 ሰው ከራሱ ጋር

በምዕራፍ ሁለት ለማየት እንደተሞከረው ሰው ከራሱ ጋር የሚያደርገው ግጭት  በልብ ወለድ ውስጥ ያሉት ገፀ-ባህሪያት ከራሳቸው ጋር በተለያዩ ጉዳዬች ዙሪያ ሲጣሉ፤ እራሳቸውን በጥፋተኝነት ስሜት ሲወቅሱ፤ በተለያዩ ጉዳዬች ላይ መወሰን አቅቷቸው አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ ከእራሳቸው ጋር ሊጣሉ ይችላሉ። ላይላ ለእርሷ የሚታያት ነገር ለሌሎች ስለማይታያቸው ለምሳሌ የጠፋ እቃ የት እንዳለ ለሷ ይታያት ስለነበር እቃው ያለበትን ቦታ ስትናገር ጎረቤቶቻቸው ሰርቃ ነው የሸሸገችው በማለት በጎረቤቶቿ እንደ ሌባ ትታይ ስለነበረ እሷም ወድጄና ፈቅጀ ያደረኩት ይመስል ለምን ሰዎቹ ይጠሉኛል በማለት እራሷንም እንደማይጠቅም ሰው በመቁጠር ከራሷ ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ትገባለች። እንድሁም የእንቁጣጣሽ ባለቤት አይምሮው ተረብሾ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት በመንፈስ ተጉዞ በነበረበት ወቅት በከፍተኛ የአዕምሮ መረበሽ ምክንያት ከራሱ ጋር ይጋጫል። ይህንን እንደማስረጃነት ጠቅሰን እንመለከታለን።

"ኹሉም ነገር አስፈራኝ! ያ ሁሉ የብርሀን ድስኩር የት ገባ? 'ከጨለማ ጋር ስፋጠጥ ትጥቅ ይሆነኛል!' ስል ያግበሰበስኩት፣ በመኖር እና በመከወን ያደረጀኹት ጥበብስ ከውስጤ በየት በኩል አፈትልኮ ይሆን ለጥልቅ ፍርሀት ያስረከበኝ በስጋ የቱ ጋር ነኝ? በመንፈስስ የቱ ጋር ነው ያለሁት? የማየው የዛሬውን ይሁን የትናንትን፣ አሊያም የነገውን አለም እስኪምታታኝ ድረስ ድቅድቅ ጨለማ ውጦኛል።" /ገፅ፡ 18/

ይህ ማለት ሰውየው በመንፈስ ተጉዞ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት በሚጥርበት ወቅት በፍርሀት ተወጥሮ ህይወቱ ጨለማ ውስጥ ያለ እስኪመስለው ድረስ ለምን እዚህ መጣሁ? በማለት ከራሱ ጋር ሲጋጭ እንመለከታለን።

### 3.1.2.5.2 ሰው ከሰው ጋር

ሁለቱ ዛፍ ቆራጮች በአንድ ድርጅት ተቀጥረው በቆረጡት ዛፍ ብዛት ክፍያ ስለሚሰጣቸው ዛፎችን ቆርጠው ከጨረሱ በኋላ ብዙውን እኔ ነኝ የቆረጥኩት በማለትበሁለቱም መካከል እርስ በርስ አለመግባባት ተፈጥሮ ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ገብተው ነበር። ይህን እንደማስረጃነት ጠቅሰን እንመለከታለን።

"አውራው ሸንጎ እንዲያያቸው የቀረቡት ሶስት ጉዳዮች ቢሆኑም አንደኛው ግን ይበልጥ አስደነቀኝ። በሁለት ዛፍ ቆራጮች መካከል የተነሳ አለመግባባት ወደ ፀብ አምርቶ ነው። ዛፍ ቆራጮቹ ለአንድ ድርጅት ዛፍ ለመቁረጥ የተቀጠሩ ሲሆኑ ክፍያቸውም የሚሰላው በቆረጡት የዛፍ ልክ ነው።

እንግዲህ ማምሻው ላይ በየድርሻቸው 'ቆረጥን!' የሚሉት የዛፍ ቁጥር ነው እሰጥ-አገባ ውስጥ የዶላቸው። በዚህም ሳቢያ ገላጋይ መሀላቸው ባይገባ ኖሮ ደም ለመፋሰስም ቀርበው ነበር።"/ገፅ፡ 64/

ሁለቱ ዛፍ ቆራጮች በቆረጡት ዛፍ መጠን ምክንያት ከፍተኛውን እኔ ነኝ የቆረጥኩት በማለት የከረረ ግጭት ውስጥ ገብተው ነበር፤ እንዲያውም ሰው በመካከላቸው ገብቶ ባያረጋጋቸው ኖሮ ግጭቱ ከሮ እስከመገዳደል የደርሱ ነበር። ሰው ከሰው ጋር የሚያደርገው ግጭት አንድ ሰው ምኞቱን እና ፍላጎቱን ለማሟላት ሲል የሚያደርገው ትግል የሌላኛውን ሰው ምኞት እና ፍላጎት ሲጨን የሚፈጠረው ግጭት ነው። በዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ በሁለቱ እንጨት ቆራጮች አለመግባባት ምክንያት ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ገብተዋል።

ሌላኛው ደግሞ ላይላ ከመጀመሪያ ባሏ ለመውለድ ፍቃደኛ ባለመሆኗ እና ባሏ ታሞ ሆስፒታል በገባበት ወቅት በባሏ እናት በተጠነሰሰ ሴራ የባሏ ቤተሰቦች ከፍተኛ ድብደባ አድርሰውባት እስከ ሳምንት ድረስ አስተኝቷታል። እንደማስረጃ ጠቅሰን እንመልከት፡-

"የሚገርምህ ደግሞ፥ ይህ ወሬያቸው በተቀጣጠለበት ወቅት ባለቤቴ ታሞ ተኛ። 'ሆስፒታል' ለአስራ ሶስት ቀናት ከተኛ በኋላ ቤት ሆኖ ህክምናውን እንዲከታተል ተብሎ ወጣ፤ እናትየው ግን ከሌሎች ዘመዶቻቸው ጋር ሆነው 'የተደረገበትን መድሀኒትማ መች ዘመናዊ ሀኪም ያገኘዋል?' እኔንም አስደብድበው ባለቤቴን 'መተት ይፈታሉ' የተባሉ አዋቂዎች ጋር በደከመ ጉልበቱ ይዘውት ይዞሩ ገቡ። በድብደባቸው በደረሰብኝ ጉዳት ሳቢያ እናቴ ቤት ተመልሼ ከሳምንት በላይ ተኛሁ። ባለቤቴም በታመመ በወሩ አረፈ።..."/ገፅ፡ 81/

ላይላ በወጣትነት እድሜዋ ካገባችው ከመጀመሪያ ባሏ እንድትወልድ የባሏ ቤተሰቦች ይነዘንዟት በነበረበት ወቅት አልወልድም ብላ በተቀመጠችበት ጊዜ ባለቤቷ ታሞ ሆስፒታል ይገባል፤ ሆስፒታል በገባበት ወቅት መድሀኒት ሰጥታው ነው እንዲታመም ያደረገችው በማለት ላይላ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰውባታል።

## 3.1.2.5.3 ሰው ከተፈጥሮ ጋር

ይህ የግጭት አይነት በልብ ወለድ ውስጥ ገፀ ባህሪያት ከተለያዩ የተፈጥሮ ክስተቶች ጋር እንዲሁም እንደሚከተሉት ሀይማኖት ከአማልክቶች ወይም ከፈጣሪያቸው ጋር የሚጋጩበት የግጭት አይነት ነው። ላይላ ሁለት ባለቤቶቿን በሞት በመነጠቋ ምክንያት በእድለ ቢስነቷ ከማዘን ይልቅ የአካባቢው ማህበረሰብ አድማ ይዘው ባገለሏት ጊዜ ፈጣሪዋ እንድወስዳት ስታማርር እና ስትጋጭ አማላኳንም አብዝታ ትወቅሳለች። እንደማስረጃነት ስንወስድ በገፅ 48 የተገለፀውን እንመለከታለን።

"የጠየኩት አንድ ነገር ብቻ ነው፤ 'በቅቶኛል፣ ደክሞኛልና ልሂድ' ነው ያልኩት። ወደማይቀርበት አለም። እርሱንም ሞከርኩ፤ እምቢ አለኝ። አላህ አልፈቅድ አለኝ። ምን ፈልጎ ይሆን ከኔ? ... ግራ ገብቶኛል።..

"ሀፍረት እና ደዌ ከላይ እስከታች የወረሳትን ልጅ ከእሷ 'ምን አገኛለሁ?' ብሎ ነው እንዲህ የሚያንገላታት? እውነት ግራ ገባኝ'ኮ።"/ገፅ፤48/

ይህ ማለት ላይላ ከሁለት ባሎቿ ሞት በኋላ ሁሉም ሰው ስላገለላት መሞት ፈልጋ አምላኳን እንዲወስዳት እየተማፀነች እና ባለመሞቷም አምላኳን "ከእኔ ምን ፈልገህ ነው የማትወስደኝ" በማለት ከአምላኳ ጋር ስትጋጭ ያሳየናል።

## 3.1.2.6 ዮቶር2 ረጅም ልቦለድ ጭብጥ

በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ እንደተሞከረው ጭብጥ ማለትደራሲው በልቦለዱ ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክ ወይም የሚያስተላልፈው መልዕክት ነው። አጥኝው የዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ አብይ ጭብጥ ብሎ የወሰደው ድፍረትን ነው። ተራኪው በፍራቻ ምክንያት በሚፈልገው የስኬት ጥግ አለመድረሱ የራሱን የህይወት ታሪክ እየገለፀ ፍርሀት ምን ያክል ከአላማችን ሊያሰናክለን እንደሚችል፣ የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት ፍርሀታችን እና አልችልም ባይነታቸው አላማችንን በማሰናከል በጎሰቆለ ህይወት ውስጥ እንደሚከተን እና ፍርሀታችንን ዋጥ አድርገን የሚደርሱብንን ፈተናዎች በትዕግስት እና በድፍረት ካደረግንእራሳችንን በፈለግነው የስኬት ማማ ውስጥ እንደምናገኘው ይገልፅልናል። ይህን እንደማስረጃነት ጠቅሰን እንመልከት።

"ፍርሀት ነፍስን ያጫጫል፣የግንዛቤን፣ የእውነትን መንገድ ያጨልማል። የመራብ እና የመጠማት ፍርሀት፣ የብቸኝነት እና የመገለል ፍርሀት፣ የመውደቅ እና የመሸነፍ ፍርሀት፣ የመኖር ፍርሀት፣ የመሞት ፍርሀት... ለቁጥር የታከቱ የፍርሀት አይነቶችን በአንድ ነፍሳችን ላይ ጭነን የምንጓዝ ፍጡራን ነን እኮ። ምን ያልፈራነው፣ ምንስ የማንፈራው አለን?

"ተመልከት፤ የመሞት ፍርሃታችንን ሞትን ባለመገንዘብ ነው የወለድነው። ሞት ማለት በዚህ ህይወት እና በሌላኛው አይነት ህይወት መካከል ያለ ጎዳና ነው፤ ወደ ሌላኛው ህይወት የሚያደርስ መንገድ። ይህን ባለመገንዘብ ብቻ በፍራቻ ታስረን ነፍሳችንን አቀጭጨናት ኖርን።"/ገፅ፡ 147-148/

ይህ ማለት ፍርሀታችንን እስካላስወገድነው ድረስ አላማችን ሀሳባችን ከሽፎ እንደሚሰናከልብን፣ እራሳችንን ያልሆነ ቦታ እንደምናገኘው እና ጨለማ ውጦን እንደሚቀር ያሳያል።

ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ በውስጡ ብዙ ንዑስ ጭብጦችን የያዘ ነው። ሁለቱ ዛፍ ቆራጮች በተጋጩበት ጊዜ በአካባቢው ባህላዊ የፍርድ ሸንጎ ስለነበር ሁለቱን ከመገዳደል ወደ እርቅ ያመጡበት ዘዴ በጣም ጥሩ ስለሆነ እንደዚህ አይነት ባህላዊ ሸንጎዎች በሀገራችን በብዛት ቢለመዱ ታላቅ የትውልድ ማፍሪያ እንደሚሆን ያሳያል። እንዲሁም በተሳሉ እና ባልተሳሉ መዶሻዎች

በመመርኮዝ አስተሳሰባችንም ከጊዜው ጋር አብሮ መሄድ እንዳለበት፤ ያለፈውን መጥፎ የህይወት ታሪክ በማንሳት የፊቱ አላማችን ላይ እንቅፋት እንዳይሆን መጠንቀቅ እንዳለብን ያሳያል።

### 3.1.2.7 ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ አንፃር

ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ የተጠቀመው አንፃር አንደኛ መደበኛ አንፃር በመባል ይታወቃል። ይህን የአንፃር አይነት በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ተራኪው ‹‹እኔ›› ይህን አየሁ ይህን ተመለከትኩ እገሌ የሚባለው ገፀ ባህሪ በዚህ ወጣ በዚያ ወረደ እገሌ ደግሞ እንዲህ ያለ ችግር ደረሰበት እገሌ እና እገሌ ተፋቀሩ፣ተጣሉ ወይም በራሴ ላይ እንዲ ያለ ድርጊት ተፈፀመብኝ እያለ የሚተርክልን የአንፃር አይነት መሆኑን ተገልጿል። ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድ ታሪኩ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ ተራኪው "እኔ" እያለ የሚጨርስልን ሲሆን አጥኚው ልቦለዱን ከአንደኛ መደብ አንፃር አስቀምጦታል።

# ምዕራፍ አራት

# ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሐሳቦች

## 4.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ዮቶር 2 ረጅም ልቦለድን ከረጅም ልቦለድ አላባዊያን አንፃር ተተንትኗል። አጥኚው ስለ ረጅም ልቦለድ አላባውያን የተመለከተ ሲሆን የፈጠራ ስራ መተንተን ከሚኖራቸው ጠቀሜታ አንፃር የዘርፉ ምሁራን ያስቀመጡትን ሀሳቦች ተጠቅሟል። የልቦለድ አላባውያን በዋናነት ልቦለዱን የሚያራምዱ ዋና አካል ናቸዉ። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በልቦለዱ ውስጥ አላባዉያን እንዴት እንደተዋቀሩ መግለፅ ነው። አንድ ልቦለድ የልቦለድ አላባውያን ካላሟላ ልቦለድ መሆን አይችልም። አንድ የልቦለድ ፀሀፊ የልቦለድ አላባውያንን በአግባቡ ማወቅና መጠቀም ይኖርበታል። በምዕራፍ አንድ የልቦለድ ምንነትን በመግቢያ እና በጥናቱ ዳራ ላይ ተብራርቷል፤ አጥኝው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ እንድሰራ ያነሳሱት ምክንያቶችና ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ምን አይነት ጥቅም እንደሚኖረው አብራርቷል። እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት የልቦለድ ምንነትን እና የረጅም ልቦለድ አላባውያንን ማለትም መቼት፣ ሴራ፣ ጭብጥ፣ ገፀ ባህሪ፣ አንፃር፣ ግጭትና ታሪክን በሚገባ አብራርቷል። በመጨረሻም በምዕራፍ አራት ላይ ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦችን አስቀምጧል። በአጠቃላይ የረጅም ልቦለድ አላባውያን ማለትም ታሪክ፣ አንፃር፣ ገፀ ባህሪያት፣ መቼት፣ ሴራ፣ ግጭትና ጭብጥ በልቦለዱ ውስጥ እንዴት እንደተጠቀማቸው በትንተናው ተቀምጠዋል።

## 4.2 የመፊትሄ ሀሳቦች

1. በረጅ ልቦለድ ውስጥ ገፀ ባህሪዎች የማይስማሙበትን ወይም የግጭታቸው መንስኤያቸው ለአንባቢያን ግልፅ እንዲሆን ጎልተው መታየት አለባቸው።

2. የረጅም ልቦለድ ፀሀፊ ልቦለድ በሚፅፉበት ወቅት የልቦለድ አላባውያን በአግባቡ ማዋቀር አለባቸዉ።

3. ልቦለድ በውስጡ ብዙ ጭብጦችን የያዘ ቢሆንም ከሁሉም ደግሞ አጠቃላይ ጭብጡ ጎልቶ መታየት ስላለበት ረጅም ልቦለዶች አጠቃላይ ጭብጣቸው ከውስን ጭብጦቹ ጎልቶ መታየት አለበት።

# ዋቢ መፅሀፍ

ዘሪሁን አስፊው፣ ( 2007)፣ የስነ ፅሐፌ መሰረታውያን፣ በንግድ ማተሚያ ዴርጅት ታተመ፣ አ.አ

አለም እሸቱ። (1994)። መሰረታዊ የምርምር እና ዘገባ አፃፃፍ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አ.አ

አማረ ማሞ። (1968)። የልብ ወለድ ድርሰት አፃፃፍ መሰረታዊ መመሪያዎች

ፋንታሁንእንግዳ። (2005)፣ የተዉኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ አ.አ

ዘሪሁን አስፋው። የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን፣ (2002)፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ